# የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
Ethiopian Broadcasting Corporation


ቁጥር ኢብኮ/6-2/3ዐ4/170

ቀን ሠኔ 0 4 2014

ለአለምአቀፍ የደረቅ አካባቢዎች ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

<u>አዲስ አበባ</u>

በግንቦት 10 ቀን 2014 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ኢብኮ07/115/739 በተደረገ የውል ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ላይ ፕሮግራም ለሕዝብ ያስተላላፋችሁበትን የአየር ጊዜ ኪራይ ክፍያ እንድትፈጽሙ በኢንቮይስ ቁጥር 05822 ከዚህ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ ልከናል፡፡

በመሆኑም የተጠየቀው ጠቅላላ ክፍያ ብር <u>150,000.00/አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር ብቻ/</u>መሆኑን እየገለጽን የሂሳብ መጠየቂያ ኢንቮይስ እንደደረሳችሁ በባንክ ሂሳብ ቁጥራችን 1000163846814 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኢ.አ ቅርንጫፍ ወይም በኮርፖሬሽናችን ገንዘብ ሰብሳቢ በወ/ሪት ረድኤት ፋንታሁን በኩል በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ስም በደረሰኝ ክፍያ እንድትፈጽሙ እየጠየቅን ለሚደረግልን ትብብር ሁሉ ምስጋናችንን እያቀረብን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር(Withholoding tax) ተቀናሽ እንደማይደረግብን እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አበራ እርቄ
እና የዱ.ቤ ክትትል
ዲፓርትመንት ኃላፊ

<u>ግልባጭ</u>

- ለደንበኞች አገልግሎት ማስተባበሪያ
- ለዱ.ቤ ክትትልና ኢንቮይስ ዝግጅት ማስተባበሪያ
- ለገቢ ፣ ተከፋይ ሂሣብና ላይሰንስ ፊ ማስተባበሪያ
- ለኮንትራት ማኔጅመንት ማስተባበሪያ
- ለወ/ሪት ረድኤት ፋንታሁን

<u>የኢ.ብ.ኮ</u>


ፖ.ሳ ቁጥር 5544 ☏ + 011--517-25-38 Fax 011-5-51-83-81

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
Ethiopian Broadcasting Corporation

ቁጥር Ref.No
ቀን Date

ለ፡-አለምአቀፍ የደረቅ አካባቢዎች ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት/ICARDA/
አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፡- ውል መላክን ይመለከታል

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እና አለምአቀፍ የደረቅ አካባቢዎች ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት/ICARDA/ አርብቶ/አርሶ አደሮች አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን እንዲያውቁ እና እንዲተገብሩ መረጃ ለመስጠት የሚረዱ ስድስት የ20 ደቂቃ የሬድዮ ፕሮግራሞችን ለማሰራት እና በብሔራዊ ሬድዮ ላይ ለማስተላለፍ የተገባ ውል ስምምነት ተፈርሞ መላኩን በትህትና እናሳውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

- ለገበያ ልማት ዲቪዥን
- ለፋይናንስ አስተዳደር ዲቪዥን
- ለሀብት ኪራይ ማስተባበሪያ
- ለብሔራዊ ሬድዮ አማርኛ ክፍል(ኮፒ)
- ለሕግ ነክ ጉዳዮች ዲፓርትመንት(ኮፒ)

ኢ.ቢ.ሲ

ፖ.ሣ.ቁ 1020 ☎ +251115513418 E-mail ebcspo@gmail.com ኢቢኮ - የብዝሃነት እና የህዳሴ ድምጽ
P.O.Box 5544 Fax +251115513453 Website www.ebc.et EBC - Voice of Diversity and Renaissance

0437

# ኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን አለምአቀፍ የደረቅ አካባቢዎች ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት /ICARDA/ ጋር የተደረገ የአየር ጊዜ ኪራይ ውል

## ክፍል አንድ

## ስለተዋዋይ ወገኖች እና ስለውሉ ዓላማ

### አንቀፅ 1

### ስለተዋዋይ ወገኖች

አገልግሎትፈላጊ :-አለምአቀፍ የደረቅ አካባቢዎች ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት /ICARDA/

አድራሻ ---------------- አዲስ አበባ

ክፍለ ከተማ ቦሌ

ወረዳ 12/13

ስልክ :0920882562/0943024337----------- 0116175580/0116172281

5689

ፖ.ሣ.ቁ -----------------

አገልግሎት ሰጪ :- የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

አድራሻ ---------------- አዲስ አበባ፣ ክፍለ ከተማ ልደታ ፣ ወረዳ9

ስልክ ቁ. -------------- 0115-153278፣0115-150310፣

ፋክስ ቁ.--------------- 0115-513418

ፖ.ሣ.ቁ ----------------- 5544

### አንቀጽ 2

### የውሉ ዓላማ

አገልግሎት ፈላጊ- አለምአቀፍ የደረቅ አካባቢዎች ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት/ICARDA/ አርብቶ/አርሶ አደሮች አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን እንዲያውቁ እና እንዲተገብሩ መረጃ ለመስጠት የሚረዱ ስድስት የ20 ደቂቃ የሬድዮ ፕሮግራሞችን ለማሰራት እና በብሔራዊ ሬድዮ ላይ ለሕዝብ እንዲተላለፍለት ከአገልግሎት ሰጪ ጋር በመስማማቱ የተደረገ የውል ስምምነት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለተዋዋይ ወገኖች መብት እና ግዴታዎች

### አንቀጽ 3

### የአገልግሎት ፈላጊ መብትና ግዴታዎች

3.1 አገልግሎት ፈላጊ በብሔራዊ ሬድዮ እና በኤፍ. ኤም. 93.1 ላይ በሳምንት አንድ ቀን ለ20 ደቂቃ ለ6 ሳምንታት ለሕዝብ እንዲተላለፍ ከአገልግሎት ሰጪ ጋር ተስማምቷል።

3.2 አገልግሎት ፈላጊ ለሕዝብ ለሚተላለፍለት የ6 ሳምንታት ባለ 20 ደቂቃ ፕሮግራም ዝግጅትና ስርጭት ቫትን ጨምሮ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ለአገልግሎት ሰጪ ለመክፈል ተስማምቷል።

3.3 አገልግሎት ፈላጊ ለፕሮግራም ቀረጻ ስራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በጉዳዩ ላይ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች በቋሚነት ይመድባል።

3.4 አገልግሎት ፈላጊ የተመደበለትን የአየር ሰዓት በአገራዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ በቀጥታ ስርጭት ማስተላለፍ አስገዳጅ ሲሆንና በሌሎች ምክንያቶች ማለትም አገራዊና ሕዝባዊ የሆኑ ጉዳዮችን ለማስተላለፍ፣ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሆኑ ስፖርታዊ ፕሮግራሞች ሲኖሩ እና የአየር ጊዜውን በሙሉም ወይም በከፊል ለአገልግሎት ፈላጊ ባይመደብ ተቀያሪ ሰዓት ሁለቱ ወገኖች በተስማሙበት ቀንና ሰዓት ለአድማጭ ተመልካቹ እንዲተላለፍ ያደርጋል ወይም ምትክ ቀን እንዲሰጠው ተስማምቷል፡፡

OHSH1

## አንቀጽ 4
## የአገልግሎት ሰጪ መብትና ግዴታዎች

4.1 አገልግሎት ሰጪ ለ6 ሳምንታት ባለ 20 ደቂቃ አርብቶ/አርሶ አደሮች አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን እንዲያውቁ እና እንዲተገብሩ መረጃ ለመስጠት አስመልክቶ ፕሮግራም በማዘጋጀት በአማርኛ ቋንቋ በብሔራዊ ሬድዮ እና በኤፍ ኤም 93.1 ላይ ለሕዝብ ለማስተላለፍ ተስማምቷል።

4.2 አገልግሎት ሰጪ ለ6 ሳምንታት ባለ 20 ደቂቃ ፕሮግራም ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ቫትን ጨምሮ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) በአገልግሎት ፈላጊ እንዲከፈለው ተስማምቷል።

4.3 አገልግሎት ሰጪ ለአገልግሎት ፈላጊ ለሕዝብ የሚያስተላለፈው ፕሮግራም በኤዲቶሪያል ፖሊሲው መሠረት ለሕዝብ ለማስተላለፍ ተስማምቷል።

4.4 አገልግሎት ሰጪ ከአገልግሎት ፈላጊ ጋር በመተባበር እና እቅድ በማዘጋጀት ፕሮግራሙን የሚያዘጋጅ እና የሚያቀርብ ቋሚ ባለሙያ/ዎች ይመድባል፣ በደብዳቤ ያሳውቃል።

4.5 አገልግሎት ሰጪ ፕሮግራሙን ለማስተላለፍ የሬዲዮ አድማጭ በሚበዛበት አመቺ ሰአት ይመድባል፣ ፕሮግራሙን አስቀድሞ ለአገልግሎት ፈላጊ ያሳውቃል።

4.6 አገልግሎት ሰጪ ፕሮግራሙን ለማዘጋጀት የመስክ ስራ በሚያስፈልግበት ወቅት ለራሱ ባለሙያዎች የሚያስፈልገውን ወጪ በራሱ ይሸፍናል።

4.7 አገልግሎት ሰጪ በፕሮግራሙ ላይ እንደዚሁም በተቋሙ ላይ በአድማጮች የሚሰጡ አስተያየቶችን፣ ጥያቄዎች እና ጥቆማዎችን በማሰባሰብ ለአገልግሎት ፈላጊ ያሳውቃል፡፡

4.8 አገልግሎት ሰጪ ለአገልግሎት ፈላጊ የተመደበውን የአየር ሰዓት በአገራዊ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ በቀጥታ ስርጭት ማስተላለፍ አስገዳጅ ሲሆንና በሌሎች ምክንያቶች ማለትም አገራዊና ሕዝባዊ የሆኑ ጉዳዮችን ለማስተላለፍ፣ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሆኑ ስፖርታዊ ፕሮግራሞች ሲኖሩ እና የአየር ጊዜውን በሙሉም ወይም በከፊል ለአገልግሎት ፈላጊ ባይመደብ ተቀያሪ ሰዓት ሁለቱ ወገኖች በተስማሙበት ቀንና ሰዓት ለአድማጭ ተመልካቹ እንዲተላለፍ ያደርጋል ወይም ምትክ ቀን ለመስጠት ተስማምቷል፡፡

4.9 አገልግሎት ሰጪ በአገልግሎት ፈላጊ ስም ለሕዝብ ያስተላለፋቸው ፕሮግራሞች ቅጂ ለአገልግሎት ፈላጊ ለመስጠት ተስማምቷል።

04541

## ክፍል ሦስት
## አንቀጽ 5
## የክፍያ አፈጻጸም ጊዜና ሁኔታ

5.1 አገልግሎት ፈላጊ ከላይ በአንቀፅ 3.2 እና 4.2 መሠረት ለ6 ሳምንት በብሔራዊ ሬድዮ ለሕዝብ ለሚተላለፍለት የአየር ሰዓት እና የፕሮዳክሽን ዋጋ ቫትን ጨምሮ 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ስራው እንደተጠናቀቀ የሂሳብ መጠየቂያ ኢንቮይስ መሠረት በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ለመክፈል ተስማምቷል።

5.2 አገልግሎት ፈላጊ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5.1 መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክፍያውን ባይፈፅም ለእያንዳንዱ ክፍያ ለዘገየበት ቀን በህግ የተደነገገውን ወለድ ጨምሮ ለአገልግሎት ሰጪ ለመክፈል ተስማምቷል።

## አንቀጽ 6
## ውል ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

6.1 ይህ ውል ሊሻሻል የሚችለው በኢትዮጵያ የውል ህግ መሠረት ነው።

6.2 ይህ ውል የተሻሻለ እንደሆነ የተሻሻለው የውል አንቀጽ የዚህ ውል አካል ይሆናል።

## አንቀፅ 7
## የውሉ አካል ሰነዶች

ይህንን የጋራ ስምምነት ለማድረግ መነሻ የሆኑ የተዋዋይ ወገኖች የተፃፃፉባቸው ደብዳቤዎች የዚሁ ውል መነሻና የስምምነት አካል ይሆናሉ።

## አንቀፅ 8
## ከውሉ የሚነሱ አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ

8.1 በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ከዚህ ውል የተነሳ አለመግባባት ቢከሰት በውይይት እና በመግባባት ለመፍታት መቻል አለባቸው።

8.2 ተዋዋይ ወገኖቹ ከላይ አንቀጽ 8.1 በተመለከተው መሠረት አለመግባባቱን መፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የዳኝነት ጉዳዩን ለመፍታት ተስምቷል።

## አንቀጽ 9

### ውሉ በህግ የሚጸና ስለመሆኑ

9.1 ይህ ውል ከተፈረመበት ዕለት ጀምሮ በሁለቱ ወገኖች የተገቡ ግዴታዎች ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በጋራ ውል ስምምነት ፀንቶ ይቆያል።

9.2 ይህ ውል በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1675 እና 1678 መሠረት ተሟልቶ የተፈረመ በመሆኑ በዚሁ ህግ አንቀጽ 1731 መሠረት በህግ ፊት የጸና እና በተዋዋይ ወገኖች ላይ አስገዳጅነት ያለው ነው።

9.3 ተዋዋይ ወገኖች ከላይ አንቀጽ 9.1 የተመለከተው እውነት እና ትክክል ስለመሆኑ እንዲሁም ይህንን ውል ወደውና ፈቅደው የተዋዋሉ መሆኑን ከዚህ በታች እንደሚከተለው በፊርማቸው ያረጋግጣሉ።

**ስለ አገልግሎት ሰጪ**

ስም ----------------------------------------

የስራ ኃላፊነት ----------------------------------------

ፊርማ ----------------------------------------

**ስለ አገልግሎት ሰጪ ሕግ ክፍል**

ስም ----------------------------------------

ፊርማ ----------------------------------------

**ስለ አገልግሎት ፈላጊ**

ስም ዶ/ር አይናለም ሃይሌ

የስራ ኃላፊነት : ሳይንቲስት

ፊርማ ----------------------------------------

## አንቀጽ 10

### የእማኞች ቃል

### የእማኞች ስምና አድራሻ

እኛ ከዚህ በታች ስምና አድራሻችን የተዘረዘሩ እማኞች ተዋዋይ ወገኖች ይህንን ውል ወደውና ፈቅደው ሲዋዋሉ ያየን እና የሰማን መሆናችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን።

| ተ.ቁ. | ስም | አድራሻ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1. | | | |
| 2. | | | |
| 3. | | | |

